# ርእሰ አንቀፅ

# እርቃኑን የቆመ አፄ

**ከኢትዮሚዲያ ሚያዝያ 4 ቀን 2000 ዓ.ም**

*ትርጉም መላኩ ጸጋዬ መኮንን*

*አብርሃም ሊንከን እንዳሉት "ሁሉንም ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ ማታለል ይቻላል፤ጥቂቶችን ደግሞ ለሁልጊዜ ማታለልም ይቻላል፤ ሁሉንም ሕዝብ ግን ለሁልጊዜ ለማታለል አይቻልም"ይህ የሚታይ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በሚያዝያ ወር ወያኔ የተለመደ የማጭበርበር ትርኢቱን በመቀጠል ያካባቢ ምርጫ ብሎ "በኢትዮጵያ የፌዝ ትንግርት የሚታይበት ወቅት ነዉ" ሚያዝያ 5 ቀን "የአካባቢና የብሔራዊ" የማሟያ ምርጫ ተካሂዷል። በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ድምጽ ለመስጠት ተመዝግቧል ተብሏል" እልፍ አእላፍ ፓለቲካ ፓርቲዎች እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ታማኝ እጩዎች በጎደሉ ለማሟላት በመወዳደር ላይ ናቸዉ። ሕዝብ እንዲያውቅ የምረጡኝ "ክርክሮች" ተደርገዋል። የገዥዉ ፕሮፖጋንዳ የሚታመን ከሆነ፤ ሚያዝያ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ክብረ በአል ይሆናል።*

*ባለፉት ሶስት ወራት አገዛዙ የሚያካሂደውን ምርጫ ለማሳመን ብዙ ጥረት አድርጓል። ኢትዮጵያም የብዙሀን ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ያለባት፤ ግልጽና ፉክክር የታየበት ምርጫም መካሄዱን ለማሳመን የማታለል ተግባሩን በስፋት ተያይዞታል።ይህም የዓለማቀፉን ማህበረሰብ በቀላሉ የሚታለል፤ ምንም አይነት የጋራ ዕውቀት መረጃና ግንዛቤ እንደሌለው ነፈዝ መቁጠር ነው። ያልታረመ የሕዝብ ግንኙነት ተቋማቸዉን በመጠቀም ኢትዮጵያውያን በራሳቸዉ መንግስት እዉነተኛ ተሰሚነት እንዳላቸዉ ለማሰመሰልና ይህንኑ የሀስት ስራ ለማሳመን ይጥራሉ።*

*ኢትዮጵያዉያን ተገደው ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ዝም በማለታቸው እንደ አላዋቂ እና ተላላዎች ሊቆጠሩ ግን አይገባም። ድምጻቸው እንደተጭበረበረና እንደተቀሙ በዚህ ረገድም ትርኢት እየተሰራባቸው መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ።*

*ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ የዓለማቀፉ ህብረተሰብ ምርጫ ተብየዉ ታማኝነት የጎደለዉ መሆኑን በሚገባ ይረዳሉ። የሰብአዊ መብት ተመልካቹ ድርጅት (ሁማን ራይት ዎች) በቅርብ በሰጠው መደምደሚያ ላይ "የአሁኑ የማሟያ ምርጫ ዉጤት የሚያሳየዉ ምርጫ እራሱ ወከባና ስጋት በተመላበት ሁኔታ ሲካሄድ የምርጫ ድምጽ ትርጉም የለሽ መሆኑን ማረጋገጡ ነው።*

የኢትዮጵያ መንግስት የስልጣን ምንጩ የሆነው ህዝብን ማዋከብና መብት መጣስ ተግባሩን በግድ ማቆም አለበት" ድብቅ ያልሆነዉ እዉነታ ምርጫ ያለ ጠንካራ የፓለቲካ ተቀናቃኖች ዉድድር፤ የንግግር ነፃነት፤ያለ ነፃ የመገናኛ ብዙሀን እና ያለ ነፃ የፍትህ አካል መካሄዱ የሚመሳሰለዉ ቅዳሴ ያለምእመናን ወይም ትምህርት ቤት ያለ ተማሪዎች አይንት ነዉ። ወደ ምርጫዉ ሁኔታ ስንገባም መራጩችን በማስፈራራት፤ በማዋከብ ሌላውን ደግሞ በማታለያ "ምዝገባ "ማካሄድ ከዚህም ሌላ የተቃዋሚ እጩዎችን "ለመመዝገብ" ፍቃደኛ ባለመሆንና በመከልከል፤ ባንፃሩ 30 ፍፁም ልብወለድ የማስመሰያ ፓሪቲዎችን [ሮቦትስ]እንደ ተጎታች መሣሪያ የሚሳቡትን አራት ሚሊዮን የራሱን አምሳያ ተወካዮች አሰልፎ ተወዳዳሪ ብሎ ማቅረብ፤ ለምርጫው "ፉክክር" መሰል ነገር አድርገዋል እንዲባልም በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሃን ባዶ ልፈፋ በማካሄድ፤ ማፈሪያ በሆነው የአገዛዙ የኃላ ኪስ የምርጫ ቦርድ አማካኝነት ይህን መሰል የተጭበረበረ ምርጫ በማቀነባበር ሂደቱ ዲሞክራቲክ ነው ማለት አይችልም።

ምርጫን እውነተኛና ሀቀኛ የሚያደርገዉ በቅድሚያ በነፃ የተደራጁ የፖለታካ ፓርቲዎች በሙሉ ነፃነት መደራጀትና መልክታቸዉን ለመራጩ ያለማእቀብና ከምርመራ ነፃ በሆነ ሁኔታ በነፃ መገናኛ ብዙሀን ሲያስተላልፉ ነው። የፓለቲካ ፓርታዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች ለመራጩ የምርጫ ግባቸውን እንዲያሳውቁ ምንም እድል ሳይሰጧቸዉ ለይስሙላ የሚደረግ ምርጫ በዲሞክራሲ ላይ ማፌዝ ነው። በእርግጠኝነት የምናውቀው በሚያዝያዉ የምርጫ ድራማ ዋናዎቹ ተዋናያን የምርጫዉን ዉጤት አስቀድመው የወሰኑት በመሆኑ አገዛዙና ተባባሪ ፓርቲዉ" የማሸነፋቸው ጉዳይ ሳይታለም የተፈታ ነገር ነዉ። በምረጫ መጭበርበር በደል በተደጋጋሚ ደርሶ አይተነዋል።

ነገር ግን ለምንድን ነዉ አገዛዙ ምርጫዉ መጀመሪያዉኑ የተወሰነ መሆኑን ሁሉም እያወቀ ምርጫው እንዲታመንለት የሚጥረዉ? ምክንያቱም እዉነተኛ ምርጫ ለባለስልጣኖች የስጋት ምንጭ በመሆኑ ነዉ። አገዛዙንም የሚጥለው ስልት ስለሚሆን ይሰጋል። በግንቦት 1997 የተካሄደው ምርጫ አገዛዙን ጣለው፤ ጉድ አደረገው፤ ሁሉንም በጥልቀት አናጋቸዉ፤ አንቀጠቀጣቸው፤ እራሳቸዉን እንዲጠይቁም አስገደዳቸዉ "በምን ዓለም ዉሰጥ ነዉ በነፃ ምርጫ፤ ግልፅና በትክክል ውድድሮች እንዲካሂድ የተሰማማነዉ?" ሕዝብ በነፃ መሪዎቹን የመምረጥ እድል ካገኘ ፍላጎቱንና ምኞቱን ይፈፅሙልኛል ብሎ የሚያምንባቸውን ይመርጣል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ያደረገው ይህንኑ ነው። ዛሬ ከባድ ዋጋ ቢከፍልበትም ምርጫውን ያደረገው አይኑን ሳያሽ ነው። ገዥዉን መደብ ግን ጥሩ ትምህርት ስጥቶታል። ሕዝቡ እንዲህ አይነት ምርጫ መምረጥ መቻሉን መገንዘባቸው ነው በእነርሱ ዘንድ በጣም የከፋና መጥፎ ድክመት ሆኖ የተቆጠረው። ከአሁን በኋላ በምንም መንገድ 1997

አይነት እዉነተኛ ዲሞክራቲክ ምርጫ እንዲካሂድ አይፈቅዱም “አንድ ጊዜ ተቃጠል ደግመኛ ግን ተጠንቀቅ” አይነት ነዉ።

የአሁኑን ምርጫ እንድናምን የሚያደርገን ምንድን ነው? ምንም። ሁማን ራይት ዎች (የእንባ ጠባቂ ድርጅት ) እንዲህ ይላል “ይህን ምርጫ ለመታደግ ጊዜው ዘግይቷል። ምርጫው ዝም ብሎ ኢህአዴግ የአካባቢዎችን ስልጣን በገፍ ለመቆጣጠር አምሳያዎቹን የሰበሰበት ነዉ።”አገዛዙ የሚፈፅማቸዉን ማታለያዎች እየተመለከትን በመታዘብ ልንሳለቅና አንገታችንን ልንነቀንቅ እንችላለን። ነገር ግን ይህን ማድረግ የለብንም ምክንያቱም ዲሞክራሲ መሳለቂያ አይደለም። በእውነት በዲሞክራሲ ስም የይሙኑልኝ ምርጫ ሲካሄድ አይናችንን ልንጨፍን ፤ጆሮአችን ልንደፍን እና ሁልጊዜ ነገሮች ይኸው ናቸው ብለን ማለፍ የለብንም። ይህን ብናደርግ በራሳችን የህሊና ፍርድ ለዳኝነት እንቀርባለን። ዲሞክራሲ በጠራራ ፀሀይ ዳግም ሲጠለፍ ጉዳዩን ይፋ የማውጣትና የመናገር የእምነት ቃል ኪዳን አለብን።

በግድ መናገር አለብን! እውነቱን መግለፅ ይኖርብናል። እርቃኑን የወጣ እውነት ነው። “አፄዉ እርቃኑን ቆሟል” በአንድነት የተቃዉሞ ድምፃችንን ማሰማት አለብን “ይህ ምርጫ ማፈሪያ ነዉ። የተጭበረበረና የተጠለፈ ነው” በማለት ለዲሞክራሲ እዉነተኛ ምስክሮች መሆን አለብን። ለአለም እውነተኛ ዲሞክራሲ አለመኖሩን መናገር ይጠበቅብናል። በተለይ የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲ መሪዎች በነጭ ለባሾችና በፖሊስ ጆሮ ጠቢዎች በደህንነት ወኪሎች እግር በእግር ቀንና ሌት ክትትል በሚደረግበት፤ እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወዳዳሪዎችን እንዳያቀርቡ በሚዋከቡበት፤ በሚታሰሩበትና በአካል በሚደበደቡበት አሰራር እዉነተኛ ምርጫ የለም። የነፃ ጋዜጦች አዘጋጆች ዘብጥያ በማውረድ ፤ ለሕዝብ ጠቃሚ መረጃዎች በማቅረባቸዉ ከፊሎቹ ሀገር ጥለዉ በተሰደዱበት ጋዜጣቸዉንም ለህትምት እንዳይበቃ በታገዱበት እና በተከለከሉበት መፍትሄ የለሽ ደረጃ ላይ ባሉበት አሰራር ነፃ ምርጫ ብሎ ነገር የለም። መራጮች የአገዛዙን እጩዎች ብቻ ድምፅ እንዲሰጡ በሚያዋክቡበት አሰራር ትክክለኛ ምርጫ ሊኖር ከቶ አይታሰብም።

ስለሚያዚያ ምርጫ ድራማ የሚያስቀዉ ጉዳይ ደግሞ የአገዛዙ ሹማምንት ከሕዝቡ የሚደርስባቸውን ግፊት ለማርገብና ለማወናበድ ያመቻኛል ብለው ማሰባቸው ነዉ። ድርቅ በከፋበት፤ ገሀድ የሆነ ሙስና በተሰፋፋበት፤ የዋጋ ግሽፈት በናረበት፤ የግፍ ጭቆና ተጠናክሮ የሰብአዊ መብት ጥሰት በተስፋፋበት አሰራር፤በተለይ በባዶ ሆዱ ያለን ሰዉ ወንድም ይሁን ሴት ማወናበድ አይቻልም። ወንድም ሆነ ሴት የተራብ ሰዉ የተራበ ነው።

ነገር ግን ዛሬ በእነርሱ የምርጫ ቀልድ ሌሎች እንደሚያደርጉት በጣም መጠመድ የለብንም ። የራሳችን ጥያቄ አለን። የራሳችን ችግር እየተጋፈጥ

ነው ። በውጭ የምንገኘው የዲሞክራሲ ደጋፊዎች መካከል የትብብር መንፈስ ይጎድለናል። በኢትዮጵያ ሀቀኛ የሆነ ዲሞክራቲክ ማህበረሰብ ለመገንባት ድርጅታዊ ትብብርና የእስትራቴጂ ቅየሳ ያንሰናል። እውነት ይነገር ከተባለ ብዙ ጊዜ አንዱ አንዱን ሲያፈርሰው ሲሰራው ብሎም ስንነቃቀፍ ነው ጊዜአችን የሚጠፋው። የእኛ መጠላለፍ አገዛዙን በስልጣን ላይ እንዲቆይ ይረዳዋል። ወርቃማና የተጣበበ ጊዜአችንን በብሄረሰብ መደራጀት፤ በፓርቲና በፓለቲካ ልዩነት መስመር እናጠፋዋለን ። ይህም ገንዘባችንን ሀይላችንና ጥረታችንን ይበታትነዋል። አንዱ ሌላውን በማናናቅ ዝቅተኛ ደረጃ በመስጠት ሀይላችን በከንቱ ይባክናል። እኛ ስንነታረክ፤ ስንጨቃጨቅ ስንጣላ ጥፋተኞቹ ግን በሀሰት ሙያ እና በምዝበራ በአካበቱት ሀብት ስርግና ምላሹን ተያይዘውታል። በኢትዮጵያ ለወጣት ወንዶችና ሴቶች የአመራር እውቀት ማደግና የፓለቲካ ንቃት መብሰል በበቂ ሁኔታ አልተሰራም። እንደዚሁም ከእነርሱ ለሚጠበቀው የዴሞክራሲ መርህን እሴት የመጠበቅ ብሎም ለረዥሙና ጠንካራው የነፃነት፤ የዲሞክራሲና የስብአዊ መብት መከበር ትግል የማዘጋጀት ሥራ በአመሪቂ ሁኔታ አልተከናወነም። አልፎ አልፎ ግንኙነታችን በንግግር ሳይቀር ያለመቻቻልና በደም ፍላት የመነጋገርና የመግለፅ ባህሪ ይታይብናል። በጓደኞች መካከል ሳይቀር በፓለቲካ ልዩነት በፍጥነት መወጋገዝ ይታያል። በመካከላችን የሚኖረውን ተፈጥሮአዊ የሀሳብ መለያየት መቀበል ይከብደናል። ይህም ብስለት የለሽ ሂደት በዲሞክራቲክ ቤተሰቦች ላይ ስጋት መደቀናችንን ማወቅ አለብን። በርካታ የሚሰሩ ሥራዎች አሉብን።

አፄው በአደባባይ መለመላውን መቆሙን ለመሸፈን በሚያምር አልባሳት እራሱን ሸፍኖ መቅረቡ የሚያታልለው እራሱን የመሆኑን ያህል፤ የሚያዝያው ምርጫ አስተባባሪ ተዋናዮችም መገንዘብና ማወቅ ያለባቸው በምርጫው መታመን ላይ ያታለሉት እራሳቸውን መሆኑን ነው።

አብርሃም ሊንከን "ሁሉንም ሕዝብ ሁልጊዜ ልታታልል አትችልም"ያለው ልክ ነበር ነገር ግን የረሳው ነገር ቢኖር ሁል ጌዜ ማታለል የሚይቻለው እራስን ብቻ መሆኑን ነው። በአሁኑ ውቅት አጼው የተሳካለት ማንንም ማጭበርበሩ ሳይሆን እራሱን ማታለል መቻሉ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ በምንም ደረጃ የእኛን የስራ ድርሻ የመወጣቱ ሀላፊነት የእኛ ነው። አሁንም እራሳችንን ለስራ እናነሳሳ!